## ግልጽ መልእክት ለሲዳማና ለአጋር የትግል ድርጅቶችና ወገኖች

**SNLO ያቀረበዉ የሲዳማ ድርጅቶች አንድነት በSLF ተስተጓጉሏል::**

ከSNLO ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

August 20/2006

**መግቢያ**

የሲዳማ ሕዝብ በአፍሪካ ቀንድ ከሚገኙ በርካታ ብሔሮች አንዱ ነዉ:: የሲዳማ ብሔር ለበርካታ ዘመናት የራሱ የሆነ መልከአ ምድር; ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር; ኢኮኖሚያዊ ይዞታ; የዳበረ ባህልና ቋንቋ ያለዉ ሕዝብ ነዉ:: የሲዳማ ሕዝብ ከ19ኛዉ ምዕተ አመት የነፍጠኛ ወረራ እስካሁኑ የወያኔ ሥርዐት ድረስ ለዘመናት የተፈራረቁበትን የጭቆናና የአንጡራ ሀብት ዘረፋ ጦርነቶችን ለአንድም ጊዜ አሜን ብሎ ሳይቀበል በሕዝባዊ አመጽና በተደራጀ ሁኔታ እየታገለ በሺዎች የሕይወት መስዋዕትነት የሲዳማነት ሕልዉናዉን አስከብሮ ለሌላዉ ምሳሌ በሚሆን ደረጃ ራሱን በራሱ በማስተዳደር ላይ ይገኛል:: በዚህች ደቂቃም በሲዳማ ምድር የወያኔ ኢሞራላዊና ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ ሳይበግረዉ የሐምሌ 6/1997 የክልላዊ መንግስትነት ዉሳኔዉ ተግባራዊነት ከጥር 1998 ጀምሮ በብሔሩ ተማሪዎች የተቀጣጠለዉና ሕፃን አዛዉንቱ ሳይቀር መላዉ የሲዳማ ዜጋ የተሳተፈበት ሕዝባዊ አመጽና ቁጣ በሰላማዊ ተቃዉሞ መርህ እየተፋፋመ ያለዉ ፀረ ወያኔ የሲዳማ ትግልም የዚሁ የሲዳማ የዘመናት ተፈጥሮአዊና ሕገ መንግስታዊ የሆነዉ ራሴን በራሴ የማስተዳደር መብቴ ይከበርልኝ መስዋዕትነት አካልና ሕያዉ ምስክር መሆኑን ወዳጅም ሆነ ጠላት መገንዘብ አለበት እንላለን::

**የሲዳማ የማንነት ጥያቄና ተቃዉሞ ሂደት**

የሲዳማን የፀረ ጭቆናና የፀረ ዲሞክራሲ አገዛዝ ተቃዉሞ ስናነሳ ትግሉንና መስዋዕትነቱን በ3ደረጃ ከፍሎ ማየት ይቻላል::1ኛ/ በግል ወይም በቡድን 2ኛ/ በሕዝባዊ አመፅ 3ኛ/ በፖለቲካና በትጥቅ ትግል ደረጃ:: በግል ወይም በቡድንና በሕዝባዊ አመጽ ደረጃ የተደረጉትን ፀረ ነፍጠኛና ፀረ ከበርቴ የትግል ሂደቶችንና የተከፈሉ መስዋዕነቶችንና ላለፉትና ለአሁኑ ትዉልድ ያስተላለፉትን የታሪክና የማንነት አሻራ ሕያዉ መዘክርነትን ለታሪክ ፀሐፍዎች ትተን በዚች አጭር መልእክታችን በተደራጀ የፖለቲካና የትጥቅ ትግል በተሳተፉ የሲዳማ የፖለቲካ ድርጅቶች ዙሪያ በአጭሩ እናተኩራለን::

**የሲዳማ የፖለቲካ ድርጅቶች እንቅስቃሴ በአጭሩ**

ባለፉት አስርት አመታት የተቋቋሙትን የሲዳማን የፖለቲካና የትጥቅ ትግል ድርጅቶችን ስንመለከት በ1970ዎቹ የደርግን ስርአት በመቃወም ከሀገር ዉጭ በትጥቅ ትግል ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍሎ በወቅቱ የትኛዉም የደርግ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ያልተቀዳጀዉን ድል ያስመዘገበና ለበርካታ አመታት አብዛኛዉን የሲዳማን ግዛት ተቆጣጥሮ የነበረዉን የሲዳማ አርነት ንቅናቄ(SLM)ን እናገኛለን:: በሀገር ዉስጥም በደርግ መዉደቂያ አካባቢ ተደራጅቶ የነበረዉና በኃላም በሽግግር መንግስት ምስረታ ወቅት ከSLM ጋር ዉህደት የፈጠረዉ Sidaamu Manni Gashshootu Songo(SMGS} ድርጅትም ሳይጠቀስ አይታለፍም:: SLM በአሁኑ ወቅት በዉጭ ሀገር የሚያደርገዉ የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ የለዉም:: ከድርጅቱ ሊቀ መንበር በስተቀር አብዛኛዎቹ የድርጅቱ አመራርና አባላት በሀገር ዉስጥ በተቃዋሚነት ይንቀሳቀሳሉ:: በ1998 የድርጅቱ ሊቀመንበር ወደ ሀገር ተመልሶ በሚያሳዝን ሁኔታ የተነሳበትን አላማና የሲዳማን ጥቅም በሚጻረር መልኩ የወያኔን መንግስት ወግኖ ቢሰለፍም ሁሉም የSLM አመራርና አባላት እንዲሁም የሲዳማ ሕዝብ የግለሰቡን አቋም በከፍተኛ ስሜት በማዉገዛቸዉ ከሀገር መዉጣቱ ይታወቃል::

በ1990ዎቹ ከSLM ተገንጥሎ የወጣዉ Sidama Liberation Front(SLF) በሀገር ዉስጥና ከሀገር ዉጭ በፖለቲካና በትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንዳለ ይነገራል:: SLF ላለፉት አምስትና ስድስት አመታት ከተለያዩ የትግል አጋር ድርጅቶችና ወገኖች የማቴሪያል; የፋይናንሻልና የሎጅስቲክ ድጋፎች በማግኘት በመንቀሳቀስና በሲዳማ ስም ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች እዉቅና የተሰጠዉ ድርጅት ነዉ::

ሌላዉ ድርጅት SNLO ነዉ:: ግንቦት 16/1994 በንጹሃን የሲዳማ ሰልፈኞች ላይ የወያኔ አገዛዝ የፈጸመዉን አሬመኔያዊ ጭፍጨፋን; የጅምላ አፈናና እስራትን SLFና ሌሎች ድርጅቶች ለአለም ሕዝብ በማሳወቅ ረገድ የነበራቸዉ አስተዋጽኦ አናሳ መሆን ያሳዘናቸዉ የSLF አባላት የነበሩና ሌሎች በዉስጥም በዉጭም የሚኖሩ የብሔሩ ምሁራንና የሕብረተሰቡ ክፍሎች በመመካከር የሲዳማን የብሶት ጽምፅ ለአለም ለማሰማት በ2002/2003 Sidama National Liberation Organnisation(SNLO)ንን መሰረቱ::ድርጅቱ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ የግንቦት 16ቱን ጭፍጨፋ ለአለም ሀገራትና ለአለም አቀፍ ድርጅቶች በማሳወቅና ወንጀለኞቹ ለፍርድ እንድቀርቡ ሰላማዊ ሰልፍ በማስተባበርና በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት ከፍተኛ ዘመቻ አድርጓል:: በተጨማሪም SNLO በተለያዩ ጊዜያት በሲዳማና በሌሎች የሀገሪቱ ብሔሮች በተለይም በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ፀረ ዲሞክራሲ ወያኔ የሚፈጽመዉን ጭቆናና ኢሰብአዊ ድርጊቶችን በየጊዜዉና በወቅቱ የተናጠልና የጋራ መግለጫ በማዉጣትና